# መሪዎቻችንን እንምረጥ!

*ኢትዮጵያችንንም ከጥፋት እናድን!*

## ክፍል ፩

ከአቶ ስውየው

የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን የዘረኞች ሥርዓት ከነቅራቅንቦው መነጋግሎ ጥሎ አዲስ ሕዝባዊ ዴሚክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት ዝግጁ መሆኑን ዕድል ባገኘበት ወቅት ማለትም በዘጠና ሰባቱ ምርጫ በነቂስ ወጥቶ በማያሻማ ሁናቴ በዓለም ታዛቢዎች ፊት ፍላጎቱን አስመዝግቦ እቤቱ ገብቷል። በዘረኝነት ፖለቲካም ላይ ሬፈረንደም አድርጓል ብል ማጋነን አይሆንም። ይህ ደግሞ ለወያኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የዘረኝነት ፖለቲካ አቀንቃኞች በግልጽ ክስረታቸውን በማያሻማ ቋንቋ አስቀምጧል ማለት ነው። ያልገባቸው ወያኔዎችና አጫፋሪዎቻቸው፤ ሻአቢያዎች፣ ኦነጎች፣ የሶማሌ ነፃ አውጪዎች ነን ባዮች፤ አሁንም የሀገራችን ችግር የአማራው ቅኝ ገዢነት ነው የሚሉን የዘረኝነት ፖለቲካ አቀንቃኝ ቡልቻ ደመቅሳዎችና መሰሎቻቸው ብቻ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጹ በወያኔዎች ሲሰረቅ እምቢኝ ብሎ አስፈላጊውን መስወዕትነትም ከፍሎአል። ወገናችን የጎደለው ነገር ቢኖር የሕዝቡን ጩኸት ሰምቶ፣ አመኔታን ገንብቶ፣ በመካከላችን እየተነዛ ያለውን አለመግባባትና ጥርጣሬን መስመር አስይዞ፣ በተግባር ለመምራትና እንደመሪነትም ምሥዋዕትነትን በመክፈል በምሳሌነት ትግሉን የሚያስቀጥል መሪ መታጣቱ ብቻ ነው። ልብ በሉልኝ ይህንን ስል ብቃት ያላቸው መሪዎች በጊዜው አልነበሩንም፣ አሁንም የሉንም ለማለት አይደለም። በጊዜው ዕውነተኛ መሪዎች ተሰሚነት እንዳይኖራቸው ተደርጎ አስመሳዮች መድረኩን አጣበው ይዘው የሕዝቡን ትግል በተዳጋጋሚ ያስበሉበትን አሻጥር ለመጠቆም ያክል ነው። ሰሞኑንም በወኔ ድረ-ገጾች የሕዝቡን ትግል መላገጫ እንዲሆን ያደረጉትን የአንድነት ፓርቲ መሪዎች ነን ባዮች የአደባባይ የሚያቅለሸልሽ ንትርክ የተከታተላችሁ ሁሉ የምለውን ትረዳላችሁ።

አንዳንዶቻችሁ መሪዎቻችንን እንምረጥ ስላልኩ ይሄ ሰው ደኅሞ ምንድነው የሚያወራው ትሉ ይሆናል። የማወራው ስለ 2010 የወያኔ ምርጫም አይደለም። በሀገራችን የተንሠራፋውን የዘረኞች ሥርዓት ከሥሩ መንግለን በመጣል በምትኩ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረትና ኢትዮጵያዊነት እንዲያቸንፍ በምናደርገው የሞት የሽረት ትንንቅ ውስጥ ዛሬ የመሪነቱን መድረክ እየተሻሙ ያሉት ለመሆኑ እነማናቸው? ብለን ከልብ ራሳችንን ካልጠየቅን ወይም እንደኔ ዕምነት ላለፉት 18 ዓመታት ስላልጠየቅን በሚደረገው ትግል ውስጥ ሕዝቡ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ቢከፍልም ምንም የሚያመረቃ ውጤት አልመጣም ነው የምለው። ለዚህም እስኪ ከዚህ በታች ትግሉን እየመራን ነው የሚሉን ወገኖች እንዴት በአመራሩ ላይ ራሳቸውን ታዋቂ በማድረድ እንደሚያመጡ እንደምሳሌ አንዳንድ ሁኔታዎችን ላቅርብና ከዚያም በዚህ ጽሑፍ ተከታይ ማለትም ወደፊት በማቀርበው ክፍል ሁለት ታዲያ መሪዎቻችንን በምን ዓይነት እንምረጥ የሚለውንና ከመሪዎቻችን ምን እንደሚጠበቅ፣ የኛስ የተከታዮቹ ሚና ምን መሆን እንደሚገባው ያለኝን ሃሳብ ለውይይት አቀርባለሁ። አንባቢዎችም በየቤታችሁ ከምታምኑት ጋር ተወያዩበት። የሀገር የኢትዮጵያችን ጉዳይ ነውና ከልባችን ያለውን ችግር እንመርምር። የጹሑፉ መልዕክትም ለምተቻቸው ብቻ ሳይሆን ለምደግፋቸውም ጭምር እንደሆነ እንዲታወቅልኝ ማሳሰብ እፈልጋለሁ።

ከአንድ ከስምንት ወራት በፊት ይሆናል አንዲት በከፍተኛ ደረጃ አከብራት የነበረች እህት ትመራው ከነበረው አዲስ የተቋቋመ የብዙሃን ድርጅት ውስጥ በማልጠብቀው ሁናቴ ግርግር ስትፈጥር ሰምቼ ምነው ምን ነካት ይህችን ወገናችንን? ብዩ ለአንድ ወዳጄ ሀዘኔን ብገልጽለት፤ አይ ያንተ ነገር ሁሉን ማመን አለና እንዲህ ሲል አጫወተኝ። ሴትዮዋ ይሄ የመጀመሪያዋ እኮ አይደለም። ከዚህ በፊት በአካባቢያችን ውስጥ የሚንቀሳቀስ የነበረ የአማራው ድርጅት ውስጥ ግርግር ፈጥራ ከመበጣበጣቸው የተነሳ እነ ዶ/ር እጉኤ የሚባሉ ሀገር ቤት ድረስ አማራነቷን ለማረጋገጥ ከተወለደችበት አካባቢ ድረስ አስጠይቀው ነበር ብሎ ጭራሹን እንድገረም አድርጎኝ ቁጭ አለ። ከዚያም እጉኤ ከሚባለው ቤተ-ክርስቲያንም ውስጥ ግርግር ፈጥራ ምዕመናኑ እባክሽ ብለው ከቤተስኪያኑ ኃላፊነት አግልለዋታል አለኝ። አሁንም ተገረምኩኝ። ለምን ይመስላችኋል? መልሱን ለናንተው።

ከጥቂት ወራት በፊት በዕለተ ቅዳሜ በኮሎምቦስ ኦሃዮ (ሰሜን አሜሪካ) አሥራ አምስት ያክል ወገኖች እነ ዶ/ር መሳይ፣ ዶ/ር ተኮላ ሐጎስ፣ ዶ/ር ገላውዲዎስ፣ ዶ/ር ዳንኤል ክንዴ፣ ዶ/ር ሐሰን ሰዒድ፣ ተስፋዬ አስገዶም፣ ዶ/ር ስለሺ አስገዶም፣ መኮንን ቸርነት፣ ክንዴ የተባሉትን ጨምሮ በአንድ ሆቴል ውስጥ የዝግ ስብሰባ አድርገው ከጥቂት ቀናት በኋላ መግለጫ አውጥተው የኢትዮጵያን ልዑላዊነት የሚሹ የዲያስፖራ ኢትዮጵያዊያን መድረክ መመሥራታቸውንና በአከታታይም ኮንፈረነንስ እንደሚጠሩንም አስታውቀውን ነበር። አጀብ ነው ብዩ የሚያመጡልንን ለመመልከት በጉጉት እየጠበቅሁ ነው። አነዚህን ወገኖቼን ላሳሰባቸው የምወደው ግን ቅንነትም እንኳ ቢኖር እንደ ድሮ የሚተዋወቁ ሰዎች ተጠራርተው ሕዝቡን እንወክላለን ብለው ራሳቸውን መሪ አድርገው ብቅ ለማለት ከሆነ መንገዱ አልጋ ባልጋና ቀላል እንደማይሆንላቸው ነው። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ኋላ የሚኮመሰስ ነገር ሁሉ ተነቅቶበት፣ ማን ምንም እንደሆነ ኮለል ብሎ እንዳገራችን የምንጭ ውሃ ጠርቶ የሚታይበት ጊዜ ደርሰናልና።

በዚያኑ ዕለት ቅዳሜ ደግሞ በሰሜን አሜሪካ ካሊፎርኒያ ሎስ አንጀልስ አቶ አለማየሁ ገ/ማሪያም (አል-ማሪያም የፈረንጅ ስሙ ነው መሰለኝ) ስብሰባ ጠርቶ በየአካባቢያችን የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት እንመሥርት ብሎ ሃሳብ ሲያቀርብ ከተሰብሳቢዎቹ መካከል ተነስተው መሪ የለንም እርስዎ ይምሩን ተብሎ ተሞግሶ ስብሰባው መበተኑን ሰምቻለሁ። በቅርቡም ሌላ የሰብአዊ መብት አስጠባቂ ኮሚቴ ብቅ ሊል ነው መለት ነው። ይሄም ጥሩ ነው። ለነገሩማ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ (ኢሰመጉም) እኮ ነበር። እንዲያው እንደ ሰብአዊ ድርጅት ከምሥረታው ጀብሮ መሪዎቹ አድሎአዊ በሆነ መንገድ ስለተወሰኑ ወገኖች አቤቱታ ለማቅረብ ፈቀደኛ አለመሆናቸውን ለታዘብን ደግሞ ዕውን ይህ ድርጅት ስለሰብአዊ መብት በኢትዮጵያ ለመታገል የቆመ ወይስ የግለሰቦች ወደፖለቲካው መድፌክ መወንጨፊያ ነው? ብለን እንድንጠይቅ አስገድደውናል እንጂ። ምክንያት ብትሉኝ ለምሳሌ ኢሰመጉ ስለነጸጋዬ ደብተራው ደብዛ መጥፋት ትንፍሽ አለማለቱን አቀርባለሁ። ድርጅቱን መሥርተዋል ተብለው የሚነገርላቸው ፕሮፌሰር መስፍንም በተንቀሳቀሱበት ሁሉ ተጠይቀው መልስ መስጠት ፈቀደኛ ሆነው አልተገኙም። ዛሬም ድርጅቱ ስለነፀገዬ ደብተራው ደብዛ መጥፋት ትንፍሽ ማለት አልቻለም። የአልማርያምም ስለሰብአዊ መብት ድርጅት ማውራት ለሁሉም በኢትዮጵያ ላሉ የፖለቲካ እሥረኞች ካለ አድልኦ መቆም ከሆነ መልካም ነው። በተግባር የሚፈረጅ ይሆናልና እስኪ ይሁን ብዩ እጠባበቃለሁ። እስከዚያው ለአቶ አልማርያም የማቀርበው ጥያቄ አለኝ። በዚያን ዕለት ስብሰባውን የመሩት ግለ-ሰብ በደርግ ዘመነ መንግሥት ቀይ ሽብር ተብሎ ወገን በሚመተርበት ጊዜ የአንድ ክፍለ-ሀገር አስተዳዳሪ የነበሩ ናቸው ሰምቻለሁና ዕውነት ነው?

ካላይ በጠቀስኩት ቅዳሜ ደግሞ እራሳቸውን ኢሕአፓ ዴሞክራሲያ ብለው የሚጠሩት የአንጃኞች ቡድን በፓልቶክ መድረካቸው ብዙ የታወቁ የድርጅት መሪዎችንና ግለሰቦችን አሰባስበው መድረክ ብሎ በዚያኑ ሰሞን ሸር-ጉድ የተባለለት የነስዩ አብራሃ፣ ገብሩ አሥራት፣ የአንድነት ፓርቲ ግንባር ነገርን ቡራኬ ለመስጠት ቆሌው እንደራቀው ቀልቻ ሲያጓሩና እንትፍ ትፍ በሉላቸው እንመርቀቸው ሲሉን ዋሉ። በዚያኑ ሰሞን አቶ ቡልቻ ደመቅሳ የኦሮሞ ፌዴራሊስት መሪ ነኝ ባይ በቪኦኤ ብቅ ብሎ እንዳረጋገጠልን ከሆነ የዚህ ስብስብ (መድረክ የሚባለው ጉድ) ይዘት ሊሆን የሚችለው የክልል አገዛዝን ወይም እንደ ገባኝ ከሆነ የአንቀጽ 39 ደጋፊዎች ብቻ ጥርቅም መሆኑን ነው። አንጃዎቹ በመጀመሪያ ለስዩ ስብሰባ ተገኙለት ብለው እንደ ትልቅ ጀግና ክበው በህገ-ወጥ መንገድ በወሰዱት የኢሕአፓ ዋሺንግተን ራዲዮ ሲለፍፉ የተሰሙና በአንድ ወቅት ደግሞ መሪአቸው በነበረው ግለሠብ አማካኝነት በፓልቶክ ኦነጎች እያፈሩ ነው እንጂ ኢትዮጵያዊነታቸውን ያምናሉ ብለው ሊሰብኩላቸው ተነስተውም እንደነበር የትላንት ትዝታ ነው። የሚገርመኝ ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት ሳይኖራቸው የተሰበሰቡበትን የኢሕአፓ ጉባዔ ረግጠው የወጡ አናሳ የድሮ የኢሕአፓ አባላት የነበሩ አንጃኞች እኛ ኢሕአፓ ነን ብለው በየቦታው ጥልቅ ሲሉ መድረክ የሚሰጧቸው፤ ወይም ከነሱ ጋራ ንክኪ የሚያደርጉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ ግለ-ሠቦችን ስመለከት ዕውን እኚህ ስብስቦች ስለ ሕግ የበላይነት ሲሰብኪኝ እንዳምናቸው ይሻሉ ብዬ እንድጠይቅ ያደርገኛል። ያሳዝነኛልም።

በቅርቡ ደግሞ እነዚሁ አንጃኞች 5ኛ ጉባኤ አድርገናል በሚል ፈሊጥ በቪኦኤ ብቅ ያለው መሪያቸው በአደባባይ በመዋሸት የንትርኩ ምክንያት አጃችንን ለወያኔ እንስጥ መሆኑ ቀርቶ ከአመራሩ የሚከሰውን ወገን ካለፈቀድ ከኤርትራ መሪ ጋር ተገናኝቷል ሊለን ሞክሮአል። በራሱ እንደበት ከድርጅቱ የወጣበትን ምክንያት የሚገልጽበት ቅጂ ሲወጣ መልስ ከመስጠት ይልቅ አሁንም ካፈርኩ አይመልሰኝ ነገር ሆኖ መቀባጠሩን ቀጥሎአል። ድርጅታቸውን ሊያፈርሱ የተነሱትስ ዋነኛው ምክንያት አፌዳፊት ፈርመን ለወያኔነት እጃችንን እንስጥ አልነበር? እዚህ ላይ እነሱንና መሰሎቻቸውን ላስታውሳቸው የምሻው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን ለማዳን መጠቃቀስ መጀመሩን ነው። ሌላው ላስታውሳቸው የምሻው ደግሞ ስዩ አብራሃና ግብራበሮቹ መለስንና ስርዓቱን እንጠላዋለን ቢሉም እነሱም አብረው የወያኔን ሥርዓት የመሠረቱ መሆናቸውን፣ ዛሬ ተጣልተናል ቢሉም እንኳ ሚስጥራቸውን አምቀው እንደያዙ መሆናቸውን ነው። አንጃኞቹ ገልቱ ከሃዲዎች ሆነው እንጂ እነስዬ አብራሃና ገብሩ አሥራት እኮ የጓዶቻችሁን የነፀጋዬ ገ/መድህንን መዳረሻ እያውቁ እስካሁን ትንፍሽም ያላሉ መሆናቸውንና ዛሬ በሀገራችን ወያኔ ላደረሰው ጥፋት ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፋረዳቸው መሆናቸውን መሆኑን ነው።

ከላይ የጠቀስኳቸው ስብሰባዎች በተካሄዱ ሳምንት ደግሞ ስዬ አብራሃ በከረንት አፌርስ የፓልቶክ መድረድ ብቅ ብሎ መድረክ ስለሚበላው ስብስብ (ዛሬ ራሱን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ ብሎ መለስተኛ ፕሮግራም አውጥቷል) ሲገልጽልን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት ወያኔን ለመጣል በሚያደርገው ትንንቅ አመራር ሊሰጥ የሚችል አንድ አማራጭ ኃይል ሊሆን እንደሚችል ነው። እኔም ጀግናው ስዬ አብራሃ ለዚሁ ተግባር አማራጭ አውራ ነኝ ነው ያለን። ጉድ እኮ ነው። የኢትዮጵንም ልዑላዊነት በማንሳት ስለኢትዮጵያዊነት ሊሰብከን ሞክሯል። ስለ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያም ያለውን ሕልም፣ ስለመድብለ ፓርቲ ሳይቀር ሊያስተምረን ቢሞክርም በዚያ መድረክ ተስብስበው ሲያደምጡት የነበሩ ወገኖቼ ግን መጠየቅ የነበረባቸውን ጥያቄዎች ባይመልሳቸውም አቅርበውለታል። እኔም በዚያ መድረክ ተሰባስበው በተለያየ መልክ እንዴት ልናምንህ እንችላለን? አንተስ የወያኔ መሥራች አልነበርክም ወይ? እስካሁንስ ለጠፋው አትጠየቅም ወይ? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ያቀረቡትን ወገኖቼን ኮርቼባቸዋለሁ።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊነት በዚያን ሰሞን በተደረጉ የተለያዩ ስብሰባዎች ነጥቦችን አስቀጥሮ ነበር ማለት ይቻላል። ሁሉም ስለ ኢትዮጵያ ልዑላዊነት ያወራ ስለነበር ማለት ነው። ለድል ግን ብዙ ትግል፣ መተማመንን መገንባት ከሁሉም በላይ ቀራጥ መሪዎቻችን በጥንቃቄ መምረጥን ይጠይቀል። እነስዬ በሕዝቡ ዘንድ መታመንን ከፈለጉ በተለይም ደጋፊዎቻቸውና አጎብጋቢዎቻቸው እንዲገነዘቡት የሚያሻ ነገር ቢኖር፣ በመጀመሪያ ደረጃ ስዬ አብራሃምም ሆነ ገብሩ አሥራትና ሌሎችም ኢትዮጵያዊነት አንገብግቦናል የሚሉን ሰዎች ከሁሉም አስቀድመው የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅትና መሰል ድርጅቶች በኢትዮጵያ ልዑላዊነት ላይ የተጫወቱትን መርዘኛ ሚና ትክክል እንዳልሆነ በመቀበል የትግራይ ነፃ ድርጅትን በማውገዝ፤ ብሎም <u>መፍረስ አለበት</u> ብለው ሲጮኹ መሰማት አለባቸው። ከወያኔዎችም ጋር ሆነው በሥልጣን በነበሩነት ጊዜ ያደረጓትን ሁሉ መናዘዝ አለባቸው። በእኔ እምነት ይሄንን ሁሉ አድርገው እንኳ በኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ መረዳት አለባቸው። ያንን ሁሉ አድርገው እንኳ በምንም ዓይነት ለምንም ኃላፊነት በመሪነት ልናጫቸው አይገባም ባይ ነኝ። በአጭሩ ድርጅቶች፤ ቡድኖችና ግለሰቦች ለተለያየ የፖለቲካ መደላድል ሲሉ ይቅር ሊባባሉ፤ ሊሳሳሙ፣ <u>ላይፋቱ ሊጋቡ</u> ቃል ሊዳን ሊገባቡ ቢችሉም የመጨረሻውን ምሕረት ሰጪነት መብት ግን ይህንን ሁሉ በደል ተሸክሞ ለኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊተዉለት ይገባል። ለፍትህም መታገል ከዚህ ያነሰ ሊሆን ከተውንም አይችልምና። ቅንነት ካለ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሃሪ ነው። በነገራችን ላይ ይኸው መድረክ የተባለው ስብስብ በቅርቡ ባለ 64 ገጽ መለስተኛ ፕሮግራም አውጥቶ ሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ/ም አሰራጭቷልና አንባቢዎች ካለበት ፈልጋችሁ አንብቡትና ተቹበት። ምን ጊዜም የሚወጠወጠው ስለሀገራችን ነውና። በኔ በኩል ስለነስዬ ከላይ ያነሳሁትን እንዲት አዮታ አይቀይረውም።

በመጨረሻ ስለሰብአዊ ድርጅቶች ከላይ ያቀረብኩት እንዳለ ሆኖ በቅርቡ በቺካጎ ተሰብስቦ የነበረ የታዋቂ ወገኖች ስብስብ <u>Ethiopian National Priorities Consultative Process (ENPCP)</u> ውስጥ ተሰብስበዋል ከተባሉት ድርጅቶች ውስጥ ላለፉት 14 ዓመታት ካለማቋረጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ የፖለቲካ እስረኞች ካለ አድልኦ ከእነፀገዬ ገ/መድኅን (ደብተራው) ደብዛው መጥፋት እስከ ስዬ አብርሃ ካለአግባብ መታሠር ዛሬ ደግሞ ስለነብርቱካን ሚደክሳ ወይም ቴዲ አፍሮ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለን ድርጅት (የኢትዮጵያ የፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ - Solidarity Committee for Ethiopian Political Prisoners - SOCEPP http://www.socepp.de/ ) ስም አንድ ግለሠብ ካለአግባብ በመጠቀም "Solidarity Committee for Ethiopian Political Prisoners - SOCEPP - Canada (SCEPP-C)" ብሎ ዓለም የሚያውቀውን ድርጅት ስም ይዞ የስብሰባው ተካፋይ መሆንን ለተመለከትን የዚህን ስብስብ አስተባባሪዎች ምን እየሠራችሁ ነው ብለን እንድንጠይቅ ተገደናል። በተለየ በስብስቡ የተሳተፉትን የስም ዝርዝሮች ከነፕሮግራማቸው አንብቤ፤ ታዋቂ አዛውንቶች ሙያተኛ ዲፕሎማቶች ዶ/ሮ ች ተሰበሰብንበት ካሉት አንዱ አጀንዳ አንጻር ይህን ዓይነት ዓይን ያወጣ ተግባር ዓይን ለዓይን የሚያስተያየን ተግባር ነው ብለው ይገምቱ ይሆን? ስለ ሕግ የበላይነትና ስለዴሞክራሲያዊ አሠራር ጥልቅ ተመራማሪዎች ባሉበት ስብስብ መድረክ ስለሰጧቸው ገለ-ሠቦችም ሆነ ድርጅቶች ማንነት ማጠየቂያ ሳያደርጉ መድረክ መስጠትስ ሊያስጠይቅ እንደሚችል አልገባቸውም? እንዲያው ከተሰብሳቢዎቹ አንዳቸው ገንዘብ አለን ብለው አዲስ አባባ ገብተው "ኮካ-ኮላ አዲስ-አባባ" ብለው የለስላሳ መጠጥ መክፈት እንችላለን ብለው ይገምታሉ? ታዲያ እንዴት የሌሉበትን ድርጅት ሥም ይዞ የስብሰባው ተሳታፊ መሆን ይቻላል? የማን አለብን ሥራ ካልሆነ በስተቀር ማለት ነው። ይሄስ ገንቢነቱ ከምኑ ላይ ነው? ቅራኔስ የሚፈታው እንዲህ ነው ("conflict resolution")?

በዚሁ ስብሰብ ላይ ሌላም የታዋቂ ድርጅት ስም (ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት- International Ethiopian Womens' Organization (IEWO)) የሚለውን ስም ይዛ የተገኘች እህታችንም እንዳለች ከመግለጫው ለመረዳት ችዬአለሁ። እንግዲህ በአማርኛ 60 ያክል ሰዎች በተሰበሰቡበት ሲወያዩ ውለው በእንግሊዝኛ መግለጫ ማውጣታቸው ዕውን ስለወገኖቻችን የተጨነቁ ወይስ የየትኛው ዓለም አቀፍ ድርጅት ወይም መንግሥት ቀልብ ለመሳብ የተመቻቸ የግብዞች ሥራ? ብዬ እንድጠይቅ ተገድጃለሁ። ለምን ተጠራጣሪ ሆንክ ብትሉኝ ወያኔ ከመጣ ጀምሮ ስንቱ ሲመጣ ስንቱ ሲሄድ ስለታዘብኩ ስለሆነ ይቅርታ ይደረግልኝ። እስኪ እንደምሳሌ አንድ ልበላችሁ። በቅርቡ የወያኔ ጦር ቂጡ ላይ ቆጭ ብሎ የሱዳን ወታደሮች በቲሃ ሱዳን ጠረፍ ወገኖቻችንን ገደሉ የሚባል ዜና ሲመጣ ያ አንድ ሰሞን ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል የነበርው የድንበር ኮሚቴ ነኝ ባዩ ለመሆኑ የት ገባ? እናም ከላይ ላነሳሁት ጥያቄ አትፍረዱብኝ።

እንግዲህ ላለፉት አሥራ ስምንት ዓመታት እንደታዘብኩት በኢትዮጵያውያን መካከል ዕውነተኛ የፖለቲካ ክርክር ማድረግ የተነወረበት፤ በቅንነትም ስለአለንበት ሁናቴ ሊያሰረዱንም ሆነ መተክላዊ አመለካከት የሚያቀርቡ ወገኖች የሚወገዙበት፤ ውሸታሞችና ሳይገድሉ ጎፈሬዎች ግን ከሚገባቸው በላይ ገንነው መድረኩን ያጣበቡበት፤ አልፎም አባብጠው ትችት እንኳ እንዳይደረግ ተሰደብን በሚል ለቅሶ አፋችንን የሸበቡበት ጊዜ ተደርሶ ባላዋቂ መሪ ነን ባዮችና በተዘዋዋሪ መንገድ ያለው ሥርዓት እንዲቀጥል ጥረት የሚያደርጉ ኃይሎች እየተሽሎከሎኩ መሪነቱ ላይ በመንጠላጠል በሕዝቡ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እያፈሰሱና እያላገጡ፤ በመካከላችን መተማመን እንዲጠፋ እያደረጉ እንደሆነ ከመታዘብ በስተቀር እስካሁን በተግባር ለትግሉ ያበረከቱትን ያላየሁበት ዘመን ነው። በማን አለብኝነት ባዶ ቀፎ ስብስብ ይዘው ድርጅት ነን በማለት ወይም ግልጽ በሆነ መንገድ የሌሉበትን ድርጅት ስም ይዘው እኛ የእገሌ ድርጅት ነን በማለት ዓይን ያወጣ አስነዋሪ ተግባር እያደረጉ፤ የሚሠሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ቦታ እንዳይኖራቸው የማግለል ዘመቻ ከማድረግ በስተቀር ማለት ነው። ብቻ የተያዘው የሕዝቡን ጩኸት ይዞ መሮጥና እኔ እገሌ አውራ ነኝ! መሪ በሉኝ! አንቱ በሉኝ! ከማለት በስተቀር። <u>መከበር በተግባር</u> መሆኑን መረዳት የተሳናቸው ግብዞች የሚርመሰመሱበት ጊዜ ደርሰናል። በከፍተኛ ደረጃ መስዋዕትነትን የከፈለን ወገንና የትውልድ የትግል ታሪክ ሲያጣጥሉና አጣመው ሲያቀርቡ ይሰማሉ። ያ ደግሞ ተከታይ ጀግኖች ቆራጥ መሪዎች እንዳይበቅሉ የተለያዩ አቋሞችን በመያዝ መደነባበርንና መጠራጠርን በመንዛት ሕዝቡ ከትግል እንዲወጣ ረድተዋል ባይ ነኝ። በየወቅቱ እርስ በርሳቸው በሚያነሱት አንባጓሮና የውሸት ጋጋታ የማያስፈልግ ንትርክ በማጫር ከመታመሣችንና ጎራ ለይተን እንድንፋጠጥ ከማድረጋቸው በስተቀር ይሄ ነው የሚባል አማራጭ ሃሳብም ሆነ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲደረግ በመሪነት ያበረከቱት ነገር ወይም የፈየዱትን አላየሁም። ባጭሩ ትኩረታችን ከወያኔ ላይ እንዳይሆን፤ ትጥቃችንን አስፈትተውናል! የቃዊሚ መሪ ነን የሚሉን መድረኩን ያጣበቡት ይህን ይመስላሉ። እንግዲህ ከዚህ የተለየ አይተናል የምትሉ ጠቁሙኝ።

የሕዝቡ ትግልና መስዋዕትነት መና ቀርቶ ካለንበት ቦታ የደረስነው በወያኔ መሠሪነት ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ነን ብለው በቡድንም ሆነ በግለ-ሠብ ተጠራርተው ራሳቸውን በመሪነት የሚያሰቀምጡቱ ለመሆናቸው ብዙ ምሳሌዎችን ልጠቅስ እችላለሁ። እስኪ እያንዳንዳችን ወደ ኋላ መሪዎች ነን ያሉንን ሁሉ ወደ መድረኩ አመጣጣቸውን፤ የተጫወቷቸውን ሚናዎች እንመርምርና ትግላችን እንዲከሽፍ ከሆኑበት ምንክንያቶች መካከል የመሪዎች አላዋቂነት እንዳልሆነ ሳንገነዘብ እንቅር።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ሌላም ሌላም ብዙ የታዘብኩትን ከነማስረጃው ማቅረብ እችል ነበር። ግን የጽሁፉ ዋና ዓላማ መሪዎቻችንን ብጥንቃቄ መመርመር ያለንበት ጊዜ መሆኑን ለመጠቆምና ዝም ማለቱ ይብቃ ለማለት ስለሆነ በዚሁ ላብቃ። ለዚህም እንዲረዳ ከመሪዎቻችን ልንጠብቀው የሚገባውንና የኛስ የተከታዮቹ ኃላፊነትና ሚና ምን እንደሆነ በሚቀጥለው ክፍል ሁለት ለውይይት አቀርባለሁ። እስከዚያው የከርሞ ሰው ይበለን።

እምቢኝ ለወያኔዎችና ለዘረኝነት!
እምቢኝ ለሆዳሞችና ለባንዶች!
እምቢኝ ለበታኞች!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን እንደገና ያብባል!

አቶ ሰውየው ከሰሜን አሜሪካ